የቨርጂኒያ ጤና ጥበቃ መምሪያ (Virginia Department of Health) በመላ ግዛቱ የሜኒንጆኮካል (meningococcal) በሽታ ወረርሽኝ ላይ ምላሽ እየሰጠ ነው። ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት [የሜኒንጆኮካል በሽታ ወረርሽኝ ምላሽ](#) ድህረ ገጽን ይጎብኙ።

# የሜኒንጆኮካል በሽታ

## ሜኒንጆኮካል በሽታ ምንድነው?

የሜኒንጆኮካል በሽታ *በኒዩየሴሪያ ሜኒንጃይተስ (Neisseria meningitidis)* ባክቴሪያ ("ሜኒንጆኮከስ (meningococcus)" ተብሎ በሚታወቅ) ምክንያት የሚከሰት ከባድ በሽታ ነው። በበሽታው የተጠቁ ጥቂት ሰዎች እንደ ማጅራት ገትር (የአንጎል እና የጀርባ አጥንት ሽፋን እብጠት) ወይም የደም ቧንቧ ኢንፌክሽን (septicemia) የመሳሰሉ ከባድ በሽታዎችን ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ።

## ማን ነው በ ሜኒንጆኮካል በሽታ የሚጠቃው?

ማንኛውም ሰው የሜኒንጆኮካል በሽታ ሊይዘው ይችላል፣ ነገር ግን በአብዛኛው የሚከሰተው በጨቅላ ሕፃናት፣ በልጆች፣ በጉርምስና ዕድሜ ላይ ባሉ እና በወጣት ጎረምሶች ላይ ነው። ሌሎች ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡ ሰዎች ደግሞ ይህ በሽታ እንዳለባቸው የታወቀ ሰው ጋር የቤት ውስጥ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች፣ የተዳከመ በሽታ የመከላከል አቅም ያላቸው ሰዎች (ለምሳሌ ኤች.አይ.ቪ ያለባቸው ወይም ስፕሊን የሌላቸው)፣ በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች (ለምሳሌ የኮሌጅ ካምፓሶች) እና የሜኒንጆኮካል ማጅራት ግርትር በተለምዶ ወደ እሚከሰትባቸው የአንዳንድ የዓለም ክፍሎች የሚጓዙ ሰዎች ናቸው።

## የሜኒንጆኮካል በሽታ የሚሰራጨው እንዴት ነው?

*የኔይሰሪያ ሜኒንጂቲዲስ (Neisseria meningitidis)* ባክቴሪያ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው በትንፋሽ እና በጉሮሮ ፈሳሽ ልውውጥ ነው። በበሽታው የተያዘ ሰው ባክቴሪያውን በቀጥታ ወደ ሌሎች ሰዎች ፊት በመሳል ወይም በማስነጠስ፣ አንድን ሰው በአፉ በመሳም ወይም ኩባያዎችን፣ የውኃ ጠርሙሶችን፣ የመመገቢያ ዕቃዎችን፣ ሲጋራዎችን፣ ቬፖችን፣ ሊፒስቲክን ወይም የጥርስ ብሩሾችን በማጋራት ሊያሰራጭ ይችላል። ባክቴሪያው የሚተላለፈው በድንገተኛ ግንኙነት ወይም በሽታው ያለበት ሰው ያለበትን አየር በመተንፈስ ብቻ አይደለም።

## የሜኒንጆኮካል በሽታ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

ምልክቶቹ ኢንፌክሽኑ በሚገኝበት ቦታ ላይ ይመረኮዛሉ። የሜኒንጆኮካል ማጅራት ገትር በድንገት የሚከሰት ትኩሳት፣ ራስ ምታት፣ የአንገት ቁርጠት፣ ለብርሃን ስሜታዊ መሆን፣ ግራ መጋባት፣ ማቅለሽለሽ እና ማስታወክ በማስከተል ይታወቃል። አዲስ በተወለዱ ሕፃናት እና ጨቅላ ሕፃናት ውስጥ እነዚህ ምልክቶች ላይታዩ ወይም በቀላሉ ሊታዩ የማይችሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ሕፃኑ ቀርፋፋ ወይም ንቁ ያልሆነ፣ በቀላሉ የሚበሳጭ፣ የሚያስታውክ ወይም በደንብ የማይመገብ ሊሆን ይችላል። በጣም ያልተለመደ ነገር ግን በጣም ከባድ የሆነው የሜኒንጆኮካል በሽታ ሜኒንጆኮካል ሴፕቲክሚያ (meningococcal

septicemia) ነው። የሜኒንጆኮካል ሴፐቲክሚያ ምልክቶች ድካም፣ ማስታወክ፣ እጅ እና እግር መቀዝቀዝ፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ በጡንቻዎች፣ በመገጣጠሚያዎች፣ በደረት ወይም በሆድ ላይ ከባድ ህመም፣ ቶሎ ቶሎ መተንፈስ፣ ተቅማጥ እና ጥቁር ወይንጠጅ፣ ቡናማ ወይም ጥቁር ሽፍታን ያካትታል።

## የሜኒንጆኮካል በሽታ እንዴት ይመረመራል?

ምርመራውን ለማረጋገጥ የደም ወይም የአንጎል እና የጀርባ አጥንት ፈሳሽ ናሙናዎች ላይ የሚደረጉ የላብራቶሪ ምርመራዎች ያስፈልጋሉ።

## ለሜኒንጆኮካል በሽታ ሕክምናው ምንድ ነው?

የሜኒንጆኮካል በሽታ በአፋጣኝ የአንቲባዮቲክ (የጸረ ባክቴሪያ) ህክምና ያስፈልገዋል። ኢንፌክሽኑ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ በመወሰን ሌሎች ሕክምናዎችም አስፈላጊ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ለምሳሌ የመተንፈሻ ድጋፍ፣ ዝቅተኛ የደም ግፊትን ለማከም የሚረዱ መድኃኒቶች እና የተጎዳ ቆዳ ላለባቸው የአካል ክፍሎች ቁስሎች እንክብካቤ ማድረግ።

## የሜኒንጆኮካል በሽታን እንዴት መከላከል ይቻላል?

የሜኒንጆኮካል በሽታን ለሚያስከትሉ ባክቴሪያዎች ክትባቶች ይገኛሉ። የሚመከሩትን ክትባቶች ወቅቱን ጠብቀን መከተብ ከበሽታው ለመከላከል ከሁሉ የተሻለው መንገድ ነው። የቤተሰብ አባላት፣ የክፍል ጓደኞች ወይም በቀጥታ ከታካሚው የአፍ ፈሳሽ (ምራቅ ወይም አክታ) ጋር የሚገናኝ ማንኛውም ሰው በፀረ-ባክቴሪያ የሚያደርገው የመከላከያ ህክምና የኢንፌክሽኑን አደጋ ሊቀንስ ይችላል። ጥሩ የንፅህና አጠባበቅ የኢንፌክሽን አደጋን ሊቀንስ ይችላል፣ ለምሳሌ እጅን መታጠብ፣ ሲያስነጥሱ ወይም ሲያስሉ አፍንጫዎትን እና አፍዎትን መሸፈን እና ሲጋራዎችን፣ ቤፖችን፣ ሊፒስቲክን፣ ስትሮዎችን፣ ኩባያዎችን፣ የመጠጫ ብርጭቆዎችን፣ የጥርስ ብሩሾችን ወይም የመመገቢያ ዕቃዎችን አለመጋራት።

## ስለ ሜኒንጆኮካል በሽታ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

- የሜኒንጆኮካል በሽታን በተመለከተ ስጋት ካለዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።
- ለአካባቢዎ የጤና መምሪያ ይደውሉ። የአከባቢ የጤና መምሪያዎች ማውጫ በhttp://www.vdh.virginia.gov/local-health-districts/ይገኛል።
- የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከልን በዚህ ድህረ ገጽ ላይ ይጎብኙ http://www.cdc.gov/meningococcal/index.html።

መጋቢት 2024